*መመሪያ ቁጥር 04/2001 ዓ.ም.*

# *የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት መመሪያ*

የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለሕብረተሰቡ የማድረስ አገልግሎት አማራጭ፣ የመረጃ፣ የመዝናኛ እና የትምህርት ፍላጐት ማሟያ መንገድ በመሆኑ፣

ይህን የብሮድካስት አገልግሎት አማራጭ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው አሠራር መከታተልና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

የውጭ ብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራሞችን በመቀበል ለደንበኞቻቸው አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ አመልካቾችን ብቃታቸውን እያረጋገጡ ፈቃድ መስጠት በማስፈለጉ፣

በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁ. 533/99 አንቀጽ 47 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## *ክፍል አንድ*

## *ጠቅላላ ድንጋጌዎች*

### 1. *አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ "የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት መመሪያ ቁጥር 04/2001 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. *ትርጓሜ*

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. ***"የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት"*** ማለት በውጭ አገር የብሮድካስት አገልግሎቶች የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን ለማድረስ በባለፈቃዱ እና በተጠቃሚ መካከል በሚደረግ

ስምምነት ለዚሁ አገልግሎት ሲባል የተዘጋጀውን ልዩ መሣሪያ ወይም የሚስጥር ቃል በመጠቀም የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡

2. ***"አመልካች"*** ማለት የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞቹ በማድረስ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ እንዲሰጠው በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ነው፡፡
3. ***"ባለፈቃድ"*** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ፈቃድ የተሰጠው እንዲሁም ቀደም ሲል ከባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ነው፡፡
4. ***"የፈቃድ ቡድን"*** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የውጪ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞች በማድረስ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት የቀረቡ አመልካቾችን የሚመዘግብ፣ ማመልከቻዎችን በማጣራት ለበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ፣ ሲፈቀድም ፈቃዱን የሚሰጥና ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የሚያከናውን የተለያዩ ባለሙያዎች ያሉበት ቡድን ነው፡፡
5. ***"ቻናል"*** ማለት አንድ ራሱን ችሎ በምስል፣ በድምፅ ወይም በሁለቱም ቅንብር የሚዘጋጅ ፕሮግራም የሚተላለፍበት ልዩ መለያ ነው፡፡
6. ***"የተጨማሪ ቻናል ዕውቅና"*** ማለት ባለፈቃዱ ተጨማሪ የፕሮግራም ቻናልን በመጠቀም አገልግሎት ለመስጠት ሲያመለክት በባለስልጣኑ የሚሰጥ ዕውቅና ነው፡፡
7. ***"የበላይ ኃላፊ"*** ማለት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ም/ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡
8. ***"ባለስልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ነው፡፡
9. ***"ቦርድ"*** ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ቦርድ ነው፡፡
10. ***"አዋጅ"*** ማለት ስለብሮድካስት አገልግሎት የወጣው አዋጅ ቁ. 533/99 ነው፡፡
11. ***"ሰው"*** ማለት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የፈቃድ አሰጣጥ

### 3. የፈቃድ አስፈላጊነት

1. ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጠው የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም፡፡
2. የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች፣ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ከደጋፊ ሰነዶች ጋር ማቅረብ አለበት፡፡

### 4. የማመልከቻ ቅጽና ከማመልከቻው ቅጹ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች

1. ባለስልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ የማመልከቻ ቅጽ ማዘጋጀት ይኖርበታል፤
   ሀ. የአመልካቹን ስምና አድራሻ፣
   ለ. በአገልግሎቱ ሊተላለፉ የታቀዱትን ቻናሎች ዓይነትና ብዛት፣
   ሐ. ባለፈቃዱ አገልግሎቱን ለደንበኞቹ የሚያደርስበትን ዘዴ፣
   መ. አመልካቹ ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ሥራ ላይ የነበረ ከሆነ የደንበኞቹን ብዛት፣
   ሠ. ሌሎች አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎችን፣
2. አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻ ቅጹ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
   ሀ. የአመልካቹ የመመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ፣
   ለ. አመልካቹ የኢትዮጵያ ዜጐች በሆኑ ሰዎች የተቋቋመ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰነድ፣
   ሐ. አመልካቹ፣ ፕሮግራሞቹን ለደንበኞቹ ለማድረስ፣ ከውጭ አገር የብሮድካስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ጋር ያደረገው ስምምነት ሰነድ፣
   መ. የአገልግሎቱ የፕሮጀክት ጥናት /ሰነድ/፣
   ሠ. ሌሎች አመልካቹ ይጠቅማሉ ብሎ የሚያቀርባቸው ሰነዶች፣

## 5. ስለማመልከቻ አቀራረብና ተቀባይነት ስለሌለው ማመልከቻ

1. የውጪ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሰው በማናቸውም ጊዜ ለባለስልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
2. አንድ አመልካች ድርጅት፡-
   ሀ. ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን የተቋቋመ ካልሆነ፣
   ለ. ከማመልከቻው ጋር የፕሮጀክት ፕሮፖዛል አያይዞ ካላቀረበ፣
   ሐ. በአዋጁ አንቀጽ 23 መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው ሰው ከሆነ፣ ዝርዝር ማጣራት ሳያስፈልግ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል፡፡

## 6. የፈቃድ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

1. የፈቃድ ቡድኑ በአንቀጽ 5 መሠረት ያቀረበውን ማመልከቻ በማጣራት ውጤቱን ከማብራሪያ እና የውሳኔ ሐሳብ ጋር ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፤
2. የበላይ ኃላፊው የቀረበለትን አስተያየት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤
3. ፈቃድ እንዲሰጠው የተወሰነለት አመልካች ለፈቃዱ የተተመነውን ክፍያ ከፍሎ ፈቃዱን እንዲወስድ በጽሑፍ ይገለጽለታል፤
4. ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት በጊዜው ቀርቦ ክፍያውን ለፈጸመ እና በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ሰነድ ለፈረመ አመልካች ፈቃድ ይሰጠዋል፤
5. ፈቃድ እንዲወስድ በጽሑፍ የተገለጸለት አመልካች፣ ደብዳቤው በደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ በመፈጸም እና በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ሰነድ በመፈረም ፈቃዱን ካልወሰደ የተሰጠው የፈቃድ ውሳኔ ይሰረዛል፤
6. ፈቃድ የተከለከለ አመልካች፣ ፈቃድ ያላገኘበትን ምክንያት ማወቅ ከፈለገ ባለስልጣኑ ምክንያቱን በጽሑፍ ይገልጽለታል፡፡

## 7. ባለፈቃዱ በማመልከቻው ስለገለጻቸው የፈቃድ ሁኔታዎች

1. ባለፈቃዱ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው የገለጻቸው ዋና ዋና ሁኔታዎች የፈቃድ ግዴታ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡
2. ባለስልጣኑ ባለፈቃዱ በማመልከቻው የገለጻቸውን ሁኔታዎች መሰረት ያደረገ የፈቃድ ሁኔታዎች ሰነድ በማዘጋጀት ባለፈቃዱን ያስፈርማል፡፡

# ***ክፍል ሶስት***

# ***ባለፈቃድ***

## ***8. የባለፈቃድ ተግባርና ኃላፊነት***

1. ለደንበኞች የሚያደርሳቸው የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራሞች የአገሪቱን ሕጐችና የሕብረተሰቡ ጥቅም የማይቃረኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡
2. ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለውን የክፍያ ተመን እንዲሁም ማናቸውንም የክፍያ ተመኑን ለውጥ ዝርዝር ለባለስልጣኑ በየጊዜው ያስታውቃል፡፡
3. ለደንበኞች የሚያደርሳቸውን ፕሮግራሞች የቻናል ዓይነት ብዛትና ይዘት ለባለስልጣኑ ያስታውቃል፡፡
4. ለደንበኞች የሚያደርሳቸውን ፕሮግራሞች ለባለስልጣኑ ያለክፍያ ያደርሳል፡፡
5. ፈቃድ ባወጣበት የአገልግሎት ዓይነት ብቻ አገልግሎቱን ያደርሳል፡፡
6. ፈቃድ ካወጣበባቸው ቻናሎች ውጭ በሌላ ቻናል ፕሮግራሞችን ለማድረስ ከፈለገ በቅድሚያ የተጨማሪ ቻናል ፈቃድ ከባለስልጣኑ ማግኘት አለበት፡፡
7. ለባለስልጣኑ ክትትል እና ቁጥጥር ያመች ዘንድ የሥራ ቦታውን እና ለሥራው የሚጠቀምባቸውን መሣሪያዎች በተጠየቀ ጊዜ ያሳያል፡፡
8. የደንበኞቹን ብዛትና የስምምነት ጊዜውን ለባለስልጣኑ ያሳውቃል፡፡
9. ባለፈቃዱ ከደንበኛው ጋር በሚያደርገው ስምምነት ደንበኛው ፕሮግራሞችን ለሕዝብ አገልግሎት እንዳያውል ይከለክላል፡፡

## ***9. የፈቃድ ዘመን***

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጥ ፈቀድ ለአምስት ዓመት /5/ ፀንቶ ይቆያል፡፡
2. ፈቃዱ ባለፈቃዱ እና በባለስልጣኑ ስምምነት መሠረት ሊታደስ ይችላል፡፡
3. የፈቃዱ እድሳት ጥያቄ መቅረብ ያለበት የፈቃድ ዘመኑ ከማለቁ ከስድስት /6/ ወራት በፊት ነው፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የእድሳት ጥያቄ ካልቀረበ ባለስልጣኑ ፈቃዱን ለማደስ አይገደድም፡፡

## *ክፍል አራት*

## *የማመልከቻ፣ የፈቃድና አመታዊ ክፍያ*

### 10. *የክፍያ መጠን*

1. አመልካች ፈቃድ ሲጠይቅ የማመልከቻ ክፍያ ብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ ይከፍላል፤
2. አመልካች ለተሰጠው ፈቃድ የሚከተለውን የመጀመሪያ የፈቃድ ክፍያ ይከፍላል፤
   ሀ. የሬዲዮ አገልግሎት ከሆነ ብር 10,000.00 /አስር ሽህ ብር/፤
   ለ. የቴሌቪዥን አገልግሎት ከሆነ ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሽህ ብር/፤
   ሐ. የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን አገልግሎት ከሆነ ብር 60,000.00 /ስልሳ ሽህ ብር/
3. ባለፈቃዱ የሚከተለውን ዓመታዊ የፈቃድ ክፍያ ይከፍላል፤
   ሀ. የሬዲዮ አገልግሎት ከሆነ ብር 8,000.00 /ስምንት ሽህ ብር/፤
   ለ. የቴሌቪዥን አገልግሎት ከሆነ ብር 40,000.00 /አርባ ሽህ ብር/፤
   ሐ. የሬዲዮ እና የቴሌቡዥን አገልግሎት ከሆነ ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሽህ ብር/፤

### 11. *ስለክፍያ ጊዜ*

1. አመልካቹ የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ሲያቀርብ የመመዝገቢያ ክፍያ ይፈፅማል፡፡
2. ባለፈቃዱ የፈቃድ የምስክር ወረቀት ከመውሰዱ በፊት የፈቃድ ክፍያ ይፈጽማል፡፡ ዓመታዊ ክፍያ እና የእድሳት ክፍያም ይከፍላል፡፡
3. ባለፈቃዱ ዓመታዊ ክፍያውን የመንግስት በጀት ዓመት በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ ካልከፈል ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር አምስት በመቶ /5/ መቀጫ እየታከለበት ይከፍላል፡፡ ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከዋናው ክፍያ ሃምሣ በመቶ /50/ ሊበልጥ አይችልም፡፡

# ክፍል አምስት

## ፈቃድ ማገድ፣ መሰረዝና ቅሬታ አቀራረብ

### 12. ፈቃድ ስለማገድ

1. የአዋጅንና የዚህን መመሪያ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎችን የጣሰ ባለፈቃድ ፈቃድ በባለስልጣኑ ሊታገድበት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚደረግ ዕግድ በጽሑፍ ሆኖ ዕግዱ የተደረገበት ምክንያትና ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን ተገልጾ ለባለፈቃዱ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡
3. የዕግዱ ምክንያት በባለስልጣኑ በተገለጸለት በ15 ቀናት ውስጥ ባለፈቃዱ የዕግዱን ምክንያት ካስወገደ ይህንኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. የዕግዱ ምክንያት የተወገደ መሆኑን ባለስልጣኑ ካረጋገጠ ዕግዱን ያነሳለታል፡፡

### 13. ፈቃድ ስለመሰረዝ

የባለፈቃዱ ፈቃድ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

1. ባለፈቃዱ ፈቃድ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘው ያለአግባብ ወይም በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
3. ያለበቂ ምክንያት አገልግሎት መስጠቱን ከአንድ ወር በላይ ሲያቋርጥ፤
4. ባለፈቃዱ ድርጅት በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንደዘጋ ሲወሰን፤
5. ባለፈቃዱ በራሱ አነሳሽነት ፈቃድ ያወጣበትን ሥራ ሲያቆም፤
6. አዋጁ አንቀጽ 30/4/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ባለፈቃዱ ለደንበኞች በሚያደርሰው ፐሮግራም አማካኝነት ተጥሰው ሲገኙ፤
7. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 መሠረት ክፍያ ያልፈጸመ እንደሆነ፤
8. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12/3/ መሠረት የዕግዱ ምክንያት መወገዱን በጽሑፍ ያላረጋገጠ ከሆነ፤

በንዑስ አንቀጽ 13.1 መሰረት ፈቃድ ሲሰረዝ፣ ባለስልጣኑ ይህንኑ በጽሑፍ ለባለፈቃዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 14. *ቅሬታ ስለማቅረብ*

1. ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ባለፈቃድ ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሰረዘ መሆኑን ባለስልጣኑ በጽሑፍ ካስታወቀው ቀን ጀምሮ በ14 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ቦርድ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቦርዱም ለቀረበለት ቅሬታ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

# *ክፍል ስድስት*

# *ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች*

## 15. *የተጨማሪ ቻናል ዕውቅና*

1. ፈቃድ ከወጣበት ቻናል ውጪ በሌላ ቻናል የውጪ አገር የብሮድካስት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች ለማድረስ የሚፈልግ ባለፈቃድ ለተጨማሪው ቻናል ከባለስልጣኑ ዕውቅና ማግኘት አለበት፡፡
2. ባለፈቃዱ የተጨማሪውን ቻናል ጥያቄ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ባለስልጣኑ የተጨማሪውን ቻናል ጥያቄ ከመረመረ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል፤
4. ባለስልጣኑ የቀረበውን የተጨማሪ ቻናል ጥያቄ የማይቀበለው ከሆነ ምክንያቱን፣ ጥያቆው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ30 /ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ ለባለፈቃዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 16. *ለውጦችን ስለማሳወቅ*

ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ሲያደርግ ለውጦችን ባደረገ በ5 /አምስት/ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

1. የሥራ አድራሻ ለውጥ ሲያደርግ፣
2. ከውጭ አገር ብሮድካስተሮች ጋር ያደረገውን ስምምነት ሲያሻሽል፣ ወይም ሲያቋርጥ፣
3. ፈቃድ ለመውሰድ ባቀረባቸው ሌሎች መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲያደረግ፣

## 17. *የመሸጋገሪያ ድንጋጌ*

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በዘርፉ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ድርጅቶች በዚህ መመሪያ መሠረት አመልክተው ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

## 18. *<u>የተሻረ መመሪያ</u>*

በግንቦት 1999 ዓ.ም. የወጣው የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማድረስ አገልግሎት የሚመራበት መመሪያ ቁጥር 5 1999 ዓ.ም. በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 19. *<u>መመሪያው የጸና ስለመሆኑ</u>*

ይህ መመሪያ ከሰኔ 5 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡